በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የጤና ሚኒስቴር

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የጤና ሚኒስቴር

የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የጤና ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2015 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የጤና ሚኒስቴር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣

- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል:: ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የጤና ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::
ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡
የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የጤና ሚኒስቴር የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እስፖንሰርነት የትምህርት ዕድል አግኝተው ወደ ውጭ ሀገር ሄደው በመማር ላይ ለሚገኙ ሰራተኞች በመመሪያው መሰረት ግማሽ የግማሽ ወር ደመወዝ ክፍያ መፈጸም ሲገባው ሙሉ ደመወዝ ክፍያ በመፈጸም ያለአግባብ በልዩነት ብር 343,967.50 ተከፍ ተገኝቷል፡፡
2. በውሉ መሰረት ተመላሽ ያልተደረገ የትምህርት ክፍያ ብር**1,822,536.20** እና አለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ ብር 47,208.00 በድምሩ ብር1,869,744.2 ተገኝቷል፡፡
3. በወጪ የተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ ብር 3,991,854.00 ተገኝቷል፡፡
4. የተሟላ ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 4,677,134.45 ተገኝቷል፡፡
5. አለ አግባብ የተከፈለ ውሎ አበል ብር **64,350.00 ተገኝቷል፡፡**
6. ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከከፈለው ልዩ አበል ላይ የስራ ግብር ብር ብር 2,328,198.00 ሳይቀነስ ያለአግባብ የተከፈለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
7. ያልተቀነሰ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ዊዝሆልዲንግ ታክስ ብር 413,805.27 ተገኝቷል፡፡
8. ከዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢ ግዥ መፈጸም ሲገባው ከፍተኛ ዋጋ አቅራቢ ግዥ በመፈጸሙ_በልዩነት ብር136,000 ያለአግባብ የተከፈለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
9. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በድምሩ ብር 293,529.00 ካወራረደው ውስጥ፤ የሲዳማ ክልላዊ መንግስት የተለያዩ እቃዎች (የደሮ ምጥን መኖ እና የፍየል መኖ) ግዥ በመፈጸም በድምሩ ብር 37,494.00 ክፍያ የተፈጸመ ቢሆንም ንብረቱ ወደ መ/ቤቱ መጋዘን ገቢ ሳይደረግ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ንብረቱ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ወደ መ/ቤቱ መጋዘን ገቢ ሳይደረግ ያለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፤
10. ብር28,002,059.43 ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
11. .ሚዛኑን/ክሬዲት ጎኑን /side/ ያልጠበቀ ተከፋይ ሂሳብ ብር696,266.53 ተገኝቷል፡፡
12. ብር **5,928,957.25** ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ (ማስረጃ ያልቀረበለት) ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

13.ከተፈቀደው መደበኛ በጀት በላይ ብር 43,826 ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 1 እስከ 4 ከተገለጸው በስተቀር የሚኒስቴሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2015 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ያሳያሉ፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

II ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)

2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ቀርቦ በድምሩ ብር 1,121,022.76 ከተወራረደው ሂሳብ ውስጥ፤ ክልሉ የተለያዩ የጽህፈት መሳሪያ ዕቃዎች ከኡስማን መሀመድ የጽህፈት መሳሪያ ችርቻሮ ግዥ በመፈጸም በድምሩ ብር 207,250.00 ክፍያ ሲፈጽም ተከታታይ ቁጥር ያለው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ መቀበል ሲገበው በፋክቱር ደረሰኝ ክፍያ በመፈጸም ሂሳቡ የተወራረደ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

2.2 ጡረታ ለወጡ ሠራተኞች መሸኛ የኮንፈርት ግዥ በሚል ብር 68,425.00 ያለአግባብ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

2.3 ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ለ2015 በጀት ዓመት በየበጀት ፕሮግራሞቹ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው የወጪ በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ስራ ላይ ያልዋለው፤ ከመደበኛ በጀት ብር 227,704,013.50 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 1,765,696,879.31 በድምር ብር 1,993,400,892.81 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

III የህጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Issues)

3.1 ለኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ባለሙያዎች የኮቪድ 19 ወረርሽኝን በመከላከልና መቆጣጠር ስራ ላይ ለተሳተፉት ከዚህ በፊት ለኢቦላ መከላከል ይከፈል በነበረው የክፍያ መጠን ለኮቪድ 19 ወረርሽኝ አበል እንድከፈል በቀን 04/11/2012 በተያዘው ቃለ ጉባኤ በመወሰን መመሪያው ከመውጣቱ በፊትሳይፈቀድ የተከፈለ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ አበል ብር 16,072,200.00 ተገኝቷል፡፡

3.2 ለጥቃቅን ወጪዎች በጥሬ ገንዘብ መከፈል ካለበት የገንዘብ መጠን በላይ የተከፈለ በድምሩ ብር 3,493,031.00 ተገኝቷል፡፤

3.3 የገበያ ጥናት አድርጎ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑ ሳይረጋግጥ ተመሳሳይ ግዥዎችን ቆራርጦ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ግዥ በመፈጸም በድምሩ ብር **3,069,023.95** ክፍያ የተፈጸመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3.4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ሂሳቦችን ሲያወራርድ የቀረቡት ሰነዶች በአለርት ሆስፒታል እና በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ከመመሪያው ውጭ ተመሳሰይ ዕቃዎችን ያለውድድር በቀጥታ ግዥ በመፈጸም በድምሩ ብር 2,463,147.03 ፤በጤና ሚኒስቴር ብር 369,999.99 በአጠቃላይ ብር 2,833,147.02 ያለውድድር በቀጥታ ግዥ የተፈጸመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3.5 ከመመሪያ ውጭ በግንቦት እና በሰኔ ወር በብር9,122,903.31 ግዥ ተፈጽም ተገኝቷል፡፡

3.6 በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ በ2015 በጀት ዓመት በብር **16,767,694.31** የተገዙ ዕቃዎች በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ገቢ ሆኖ ክፍያ የተፈጸመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

3.7 ከተጠቃሚው የስራ ክፍል የግዥ ጥያቄ ሳይቀርብ በብር **3,879,521.00** ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

3.8 ሰኔ 30/20154 በሚታየው ሂሳብ ሪፖርት በድምሩ ብር **6,005,513,975.43** ወቅቱን ጠብቆ ያልተሰበሰበ ሂሳብ መሆኑ፣

3.9 በድምሩ ብር 20,066,615.24 በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ የተገኘ መሆኑ፣

I. ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)

3.1 ልዩ ልዩ ጉዳዮች

- ለአማራ ክልላዊ መንግስት ለሰቆጣ ቃልኪዳን ፕሮግራም የሰጠውን ገንዘብ ክልሉ ተጠቅሞበት የወጪ ሰነዱን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ አቅርቦ ሂሳቡ የሚወራረድ ሲሆን ክልሉ የተጠቀመበት የወጪ ማስመስከሪያዎች እና የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች ምንም አይነት ቁጥር የሌላቸውን ሆነው ተገኝቷል፡፡

3.2 የንብረት አያያዝን በተመለከተ

የቋሚ እና አላቂ ንብረት አመዘጋገብ፤የአያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፤

- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በ 2011 በጀት ዓመት ተገዝቶ አገልግሎት ላይ ሳይውል በአላቂ ንብረት ክፍል የሚገኝ፤ ሞኒተር ዴል ብዛት 14 ፡ አልካቴል ታብሌት 16 GB ብዛት 150፡ ሪንግ ባለ16 ሚ.ሊ ሜትር ብዛት 949 ፡ ሪንግ ባለ25 ሚ.ሊ ሜትር ብዛት 895 ፡እስኩዌር ወረቀት በደስጣ 13 ፡ ባለመስመር ወረቀት በደስጣ 6 እና፡A 3 ወረቀት በደስጣ 50 ያለአገልግሎት የተቀመጠ መሆኑ፤
- በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዋና ግቢ ውስጥ ሁለት መጋዘን ያለ ሲሆን በሁለቱም መጋዘን ውስጥ አላቂ እና ቋሚ ንብረት በአንድ ላይ የሚገኝ መሆኑና የአላቂ እና የቋሚ ንብረቶች ለቁጥጥር በማያመች ሁኔታ የሚያዝ መሆኑ፡
- በራስ እምሩ መጋዘን ውስጥ በጣም ብዛት ያላቸው ፕሪንተሮች፡ ዴስክቶፖች ፡ የፎቶኮፒ ማሽኖች፡ የላፕቶፕ ኮምፒተሮች ፡ዩ.ፒ.ኤስ.፡የመስመር ስልክ ቀፎዎች ፡ቶነሮች የተለያየ መጠን ያላቸው ቴሌቪዥኖች ፤ የሰርቨር ባትሪዎች ፤የኦዲዮ ቪዥዋል ዕቃዎች እና የተለያየ የስቴፕለር መምቻዎች በመመሪያው መሰረት መወገድ ያለበት ቢሆንም ሳይወገድ ተከማችተው የሚገኝ መሆኑ፤
- ሳር ቤት በሚገኝ የመ/ቤቱ ተመላሽ ስቶር ውስጥ የተለያየ መጠን ያላቸው በርካታ ተመላሽ የተሸከርካሪ ጎማዎች ፤ የተለያዩ መጠን ያላቸው ጠረጴዛዎች እና ወንበሮች ፤ የተለያየ መጠን ያላቸው ቁም ሳጥኖች ሳይወገዱ ከ2 ዓመት በላይ የንብረት ተመላሽ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ ከመሆኑም በላይ ተመላሽ

የተደረጉት ንብረቶች በብዛት የማይታወቅ በመሆኑ ከውስጡ ቢጠፋና ቢሰረቅ ጠፍቷል ለማለት የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት የሌለው መሆኑ፡፡

- ሰሌዳ ቁጥራቸው ኢ.ት4-12202፤ኢ.ት4-16962 ፤ኢ.ት4-12192 እና ኢ.ት4-187154 የሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ ወይም በብልሽት የቆሙ ተሸከርካሪዎች በባለሙያ ተይቶ አገልግሎት የሚሰጡ ከሆኑ ተጠግኖ አገልግሎት መስጠት ሲገባቸው ያለአገልግሎት በሳር ቤት የሚገኘው ጋራጅ ውስጥ ቆሞ የሚገኙ መሆኑ፤
- ሚኒስቴር መ/ቤቱን የለቀቁ አስራ አንድ (11) ሰራተኞች በእጃቸው የሚገኘውን በድምር ብር 335,716.21 ዋጋ ያላቸው ቋሚ ንብረቶች ሳያስረክቡ መ/ቤቱን የለቀቁ ሲሆን ንብረቱን ተመላሽ አለማድረጋቸው በመመሪያው መሰረት ለመ/ቤቱ የበላይ ሃላፊ ሪፖርት ተደርጎ የህግ ተግባር ለሚከታተል የስራ ክፍል ክትትል ተደርጎ እንዲመለስ መደረግ ሲገባው ያልተመለሰ መሆኑ፤

3.3 <u>ባለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው</u>

<u>የ2013 በጀት አመት የሂሳብና የንብረት ኦዲት ግኝቶች</u>

- በወጪ ለተመዘገበው የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከጉምሩክ ባለስልጣን የተጻፉ ደብዳቤዎች ያልቀረበላቸው እና የንብረት (የዕቃ ገቢ ደረሰኝ) ከወጪው ሰነዱ ጋር ያልተያያዘ ብር 51,823,994.57 የሚገኝ መሆኑ፡፡
- ዕቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት (የዕቃ ገቢ ደረሰኝ) ያልቀረበላቸው ብር 397,764,419.12 የሚገኝ መሆኑ፡፡
- የመ/ቤቱ አንድ ሰራተኛ ከስራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት የተጣራ ደመወዝ ብር 3,667.07 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፡፡ **(አባሪ ቁ.13.2)**

<u>የ2012 በጀት ዓመት የሂሳብና የንብረት ኦዲት ግኝቶች</u>

- ከመ/ቤቱ ከስራ ከለቀቁ በኋላ ያልሰሩበት ደመወዝ ብር 11,829.60 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኝ መሆኑ
- ብር **763,480,700.45** ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያያዝ ያልተደረገ መሆኑ::

<u>የ2011 በጀት ዓመት የሂሳብና የንብረት ኦዲት ግኝቶች</u>

- ለአምስት ሰራተኞች ከስራ ከለቀቁ በኋላ በጠቅላላው ብር 7,849.50 የደመወዝ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ
- በበጀት ዓመቱ ብር 515,335,026.21 ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያያዝ (እንዲቀርብ) ያልተደረገ መሆኑ
- በመ/ቤቱ ይሰሩ የነበሩ አንድ ሰራተኛ ከስራ በለቀቁበት ወቅት ለስራ የተረከቧቸውን ዴል ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ለንብረት ክፍል ተመላሽ ሳያደረጉ ንብረቶቹ በስማቸው የሚገኙ መሆኑ፡፡

<u>የ2010 በጀት የሂሳብና የንብረት ኦዲት ግኝቶች</u>

- ከመ/ቤቱ ከስራ የለቀቀ አንድ ሰራተኛ ከስራ ከለቀቀ በኋላ የተከፈላቸው ብር 1,479.5 ተመላሽ ያልተደረገ እና ለስራ ግብርና ለጡረታ ተቀናናሽ ሂሳቦች ደግሞ ተገቢ ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ያልተደረገ መሆኑ፡፡
- መ/ቤቱ ለሰራተኞቹ ከፈጸመው የዓመት ፈቃድ ክፍያ ላይ ብር 66,185.38 ስራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፡፡
- መ/ቤቱ በ2010 በጀት ዓመት ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በተጻፈለት ደብዳቤ መሰረት የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ አከናውኗል፡፡ ሆኖም ብር 23,969,464.20 ቀረጥ የተከፈለባቸው ዕቃዎቹ ገቢ ለመደረጋቸው የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያያዝ ያልተደረገ መሆኑ
- ከስራ ሲለቁ የተረከቡትን ቋሚ እቃዎች ያላስተላለፉ እንዲሁም ማስረከብ ያለባቸውን ደግሞ ያላስረከቡ መሆኑ፡፡

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

ሚያዚያ 2016 ዓ.ም